# በእውነት እና በተጠያቂነት ላይ የተመሰረተ የፍትህ እሳቤ፡- በከምባታ ብሔረ-ሰብ ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት መሰረት የቀረበ ምልከታ

**ይድነቃቸው አየለ ዝቅአርጌ**♣

**DOI:** https://dx.doi.org/10.4314/hujl.v9i1.9

This reflection is licensed under a Creative Commons Attribution (CC BY)

**Accepted: 10 April 2025** **Published: 20 June 2025**

**Recommended Citation:** ይድነቃቸው አየለ ዝቅአርጌ, 'በእውነት እና በተጠያቂነት ላይ የተመሰረተ የፍትህ እሳቤ፡- በከምባታ ብሔረ-ሰብ ባህላዊ የዳኝነት ሥርዓት መሰረት የቀረበ ምልከታ', *Hawassa University Journal of Law*, Vol. 9. (2025), PP. 255-271. DOI: https://dx.doi.org/10.4314/hujl.v9i1.9

## 1. መግቢያ

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት የሚገኙ ማህበረሰቦች በረጅም ታሪካዊ ሂደት፣ ትስስር፣ ያዳበሩት የጋራ ልምድ እና እሴት መሠረት የደረጁ እና ብዝሃነት ያላቸው ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች ይገኛሉ፡፡ ጤናማ እና ዘላቂ ለሆነ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ መስተጋብር እነኚህ ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች ፋይዳቸው የላቀ ነው፡፡ የህግ ብዝሀነትን እና ባህላዊ የግጭት አፈታትን በሚመለከት ኢትዮጵያ ላይ መሰረት አድርገው የሚያጠኑ ምሁራን እነዚህ ስርዓቶች ሀገራት ለሚገነቡት መደበኛ የፍትህ ስርዓት መሠረት ሊሆኑ እንደሚገባ ይጠቁማሉ፡፡[1] በተቃራኒው ኢትዮጵያ ዘመናዊ እና መደበኛ የሆነ የፍትህ ሥርዓት ለማደርጀት ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ-መንግስት (1930-1960ዎቹ) ጀምሮ ከምዕራቡ ዓለም በሰፊው የተወሰዱ ልምዶች መሰረት ዝርዝር ህግ፣ ስነስርዓት እና የፍትህ ተቋሚት ተቀርጸው ተግባር ላይ ውለዋል፡፡[2]

♣ LLB, MA, PhD, Assistant Professor at School of Law, Hawassa University, Hawassa, Ethiopia, Email: ayelezikargie@hu.edu.et

[1] John Griffiths, 'What is Legal Pluralism?' *The Journal of Legal Pluralism and Unofficial Law*, Vol. 18, No. 24 (1986), pp. 1–55; Sally Engle Merry, 'Legal Pluralism' *Law & Society Review*, Vol. 22, No. 5 (1988); Boaventura de Sousa Santos, *Toward a New Legal Common Sense: Law, Globalisation and Emancipation* (2nd ed., Butterworths, London, 2002).

[2] Abera Jembere, Legal history of Ethiopia. Hamburg and London: Lit Verlag (2000).

ይህ መደበኛ ወይም ዘመናዊ የፍትህ ስርዓት በተፃፈ ዝርዝር ህግ፣ ስነስርዓት እና የግለሰብ መብት ላይ ያማከለ ማስረጃ የማዳእጥ፣ እውነትን የማፈላለግ እና የዳኝነት አሰራርን ብቻ የሚከተል በመሆኑ አብዛኛው የኢትዮጵያ ኅብረተሰብን ዘልቆ ለመግባት እንዳልቻለ ሲነገር፤ በጂኦግራፊያዊ እና በማህበራዊ ደረጃ የራቀ፣ አገልግሎቱ ሊደረስበት የማይችል (inaccessible)፣ ብዙ ወጪ የሚጠይቅ (costly)፣ ከማህበራዊ ዘይቤ ጋር የተናጠበ (socially misaligned) እንዲሁም የተራዘመ (delayed) እና ቀልጣፋ (timely) ፍትህ በሀገሪቱ ሊያሰፍን እንዳልቻለ ይነገራል::[3]

በተቃራኒው ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች እውነትን እና ተጠያቂነትን አጣምረው የያዙ ሲሆን፤ ይህም መደበኛው የፍትህ ስርዓት ላለበት እውነትን የማጥራት እና ፍትሃዊ ተጠያቂነት በማስፈን ሂደቱ የሚያጋጥመውን ተግዳሮት ለመወጣት የሚያስችል እምቅ አቅም እንዳላቸው ይነገራል:: በዋናነት ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች መሰረታቸው ማህበራዊ ልማድ፣ የሕዝብ የጋራ ሥነ-ልቦና እሴት እና ስሜት እንዲሁም በታሪካዊ ልምዶች ላይ ነው::[4] በዚህ ስርአት ውስጥ እውነት የሚለካው በማህበራዊ ስምምነት፣ እውነታውን በአካል ተገኝተው በተረዱ ምስክሮች ወይም ባህላዊ ዳኞች እውቀት እና ተፈጥሯዊ እውነቶች ላይ ተመስርቶ ሲሆን፤ ተጠያቂነት ደግሞ በጉዳዩ ዙሪያ ያለውን ማህበራዊ ግንኙነት በመመለስ ወይም በመፈወስ ላይ ያተኮረ ነው::[5] በሌላ በኩል መደበኛ የፍትህ ስርዓቶች በተፃፉ ሕጎች፣ በማስረጃዎች እና ውስን በሆነ ዳኝነት ስርዓቶች እና ሂደቶች ላይ ብቻ የተመሰረቱ ናቸው ማለት ይቻላል::[6] በመሆኑም እውነት በመደበኛ የፍትህ ስርዓት ውስጥ የሚወሰነው በሳይንሳዊ ማስረጃዎች እና በመደበኛው ሕጋዊ ሂደቶች በኩል ሲሆን፤ የተጠያቂነት ስርዓቱ

[3] Alula Pankhurst and Getachew Assefa, Understanding Customary Dispute Resolution in Ethiopia in Alula Pankhurst and Getachew Assefa (eds.), Grassroots Justice in Ethiopia: The Contribution of Customary Dispute Resolution (Centre Français d'Études Éthiopiennes, Addis Ababa, 2008), pp. 1–76

[4] Ibid

[5] Getachew Assefa, 'Towards Widening the Constitutional Space for Customary Justice Systems in Ethiopia', *Culture and Social Practice*, No. 43 (2020).

[6] Ibid

በዋናነት በግለሰብ ላይ በሚተላለፍ እና በሚፈጸም ቅጣት ላይ ያተኩራል። በመሆኑም መደበኛ የፍትህ ስርዓቶች በጋራ ማህበራዊ ሞራል፣ እምነት እና እሳቤ ላይ የተመሰረተ እውነትን የማጥራት፣ ማህበራዊ ስምምነት የመፍጠር፣ ከግለሰብ ቅጣት ያለፈ ተጠያቂነትን የማስፈን እና ማህበራዊ ሰላምን የመመለስ ውስንነት አለባቸው። ነገር ግን እንደ ከንባታ ማህበረሰብ ያሉ ባህላዊ ዳኝነቶች እውነት እና ተጠያቂነት ማስፈን ዋነኛ ትኩረታቸው ሲሆን፤ እውነት እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ለባህላዊ ፍትህ ስርዓቶች እና ተቋሚት መሰረት ናቸው።

ከላይ የተጠቀሱትን የዘመናዊ እና መደበኛ ፍትህ ሥርዓት ክፍተቶች በባህላዊ ፍትህ ስርዓት ለመሙላት፣ በማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ተሞክሮዎች እና እውቀቶች በበቂ ሁኔታ ተጠንተው እና ተሰንደው፣ ያለባቸው የሀይል ሚዛን ልዩነት እና የስነፆታ አካታችነት እክሎች ታርመው፣ ከመሰረታዊ የሰብአዊ መብት ጥበቃዎች ጋር በማስማማት እና ከሀገሪቱ የፍትህ ስርዓት ጋር በማጣጣም ለፍትህ ስርዓቱ አጋዥ እንዲሆኑ ሲደረግ እምብዛም አይታይም።[7] አንዳንድ የሚስተዋሉ ሙከራዎች እንደሚጠቁሙት በተቆራረጠ መልኩ ክልሎች ባህላዊ የፍትህ ስርዓትን ከመደበኛው ፍትህ ስርዓት ጋር በማጣመር ቀልጣፋ እና ውጤታማ የፍትህ ስርዓት ለማስፈን ሲጣጣሩ ይታያል። በኦሮሚያ ክልል (በዋናነት አርሲ አካባቢ) እየተተገበረ ያለው ጃርሳ ቢያ ተቋም (Jaarsa Biyyaa Institution) በምሳሌነት የሚቀርብ ተሞኩሮ ሲሆን፤[8] ይህም ባህላዊ ስርዓት መሰረት ያላቸው መሪዎች እንዲሁም በብስለታቸው እና ማህበራዊ ሚናቸው መሰረት የተመረጡ ባህላዊ ዳኞች ከመደበኛ የፍትህ ስርዓት ጎን ለጎን እውነትን በማፈላለግ እና የሚነሱ ማህበራዊ ግጭቶችን እንደየአካባቢው

---

[7] Asafa Jalata, ‘Gadaa System and Oromo Resistance’ *Journal of Oromo Studies*, Vol. 19, No. 1 (2012); Getachew Assefa, ‘Towards Widening the Constitutional Space for Customary Justice Systems in Ethiopia’ *Culture and Social Practice*, No. 43 (2020); Alula Pankhurst and Getachew Assefa, Understanding Customary Dispute Resolution in Ethiopia in Alula Pankhurst and Getachew Assefa (eds.), Grassroots Justice in Ethiopia: The Contribution of Customary Dispute Resolution (Centre Français d'Études Éthiopiennes, Addis Ababa, 2008), pp. 1–76

[8] Derara Ansha Roba, ‘The Status of Traditional Dispute Resolution Institutions under the Ethiopian Legal System’ *Journal of Law and Conflict Resolution*, Vol. 15(1), July–December 2024, pp. 1–12, DOI: 10.5897/JLCR2024.0371; Derara Ansha Roba, ‘The Interplay Between Traditional Dispute Resolution Institutions and the Formal Justice System in Ethiopia: The Case of the Jaarsa Biyyaa’ *African Journal on Conflict Resolution*, Vol. 24, No. 1 (2024), pp. 47–70, https://journals.co.za/doi/full/10.10520/ejc-accordr_v24_n1_a4 accessed on 16 April 2025.

እሴቶች መሰረት ለመዳኘት አገልግሎት ሲሰጡ ይስተዋላል። ይህን መሰል የተቆራረጡ ሙከራዎች ዘርፈ ብዙ እክሎች እንዳለባቸው ምርምሮች ሲያመላክቱ፤ በዋናነት ትርጉም ያለው አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ በሚያስችል መንገድ እና እሳቤ እንዳልተዋቀሩ፤[9] ከማንነት እና የራስን እሴት ከመገንባት ሂደት የሚያናጥቡ ዘመናዊ ትምህርቶች፣ እምነቶች እና አስተሳሰቦች ሰፊ ተግዳሮት እንደፈጠሩባቸው፤[10] እንዲሁም በመደበኛ ፍርድ ቤቶች እና ባህላዊ ፍትህ ተቋማት መሀከል ያለው መስተጋብር በህግ ስርዓት እና ተሞክሮ ያልበለፀገ፣ ክፍተት ያለባቸው እና ያልተቀናጁ እንደሆኑ ይነገራሉ።[11]

በአንድ አጋጣሚ ከጓድኞቼ ጋር ስለከምባታ ብሔረ-ሰብ ባህላዊ የፍትህ ስርዓት አስመልክቶ የነበረን ውይይት ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች እውነትን እና ተጠያቂነትን ከመደበኛው ፍትህ ስርዓት በተሻለ መልኩ ለማስፈን የሚያስችል አቅማቸውን እንድጠይቅ እና ይህንን የግል ምልከታ እንድፅፍ አነሳስቶኛል። የዚህ አጭር ጽሁፍ አላማ የከንባታ ማህበረሰብን የባህላዊ ፍትህ ሥርዓት መሰረት በማድረግ፥ ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች ከመደኛ የፍትህ ስርዓት አንጻር እውነትን በተሻለ ደረጃ የማጥራት እና ተጠያቂነትን የማስፈን እምቅ አቅም እንዳላቸው ለማሳየት እና ፅንሰ-ሀሳብን መሰረት ያደረግ የፀሃፊውን ግላዊ ምልከታ ለማቅረብ ነው። በመሆኑም መደበኛ ያልሆኑ ቃለመጠይቆች እና የቡድን ውይይቶች በመጠቀም የከምባታ ህዝብ ባህላዊ የፍትህ ስርዓትን፣ ልምዶችን እና ትውፊቶች በዚህ ፅሁፍ የተዳሰሱ ሲሆን፤ ይህንን ምልከታ ለማበልጸግ እና ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች ለዘመናዊ የህግ ሥርዓት ያላቸው

---

[9] Boaventura de Sousa Santos, Toward a New Legal Common Sense: Law, Globalization, and Emancipation (2nd ed., Butterworths, London, 2002).

[10] Gosa Setu Tafese, Anwar Hassen Yunus and Gobezaychu Baye Kassa, 'The Challenges to the Informal Justice System in Ethiopia' *Journal of Law, Policy and Globalization*, Vol. 105 (2021), p.1; Yirga Gelaw, *Native Colonialism: Education and the Economy of Violence Against Traditions in Ethiopia* (The Red Sea Press, 2017).

[11] Derara Ansha Roba, 'The Interplay Between Traditional Dispute Resolution Institutions and the Formal Justice System in Ethiopia: The Case of the Jaarsa Biyyaa' *African Journal on Conflict Resolution*, Vol. 24, No. 1 (2024), pp. 47–70; Getachew Assefa, 'Towards Widening the Constitutional Space for Customary Justice Systems in Ethiopia' *Culture and Social Practice*, No. 43 (2020).

አበርክቶ እና እውነትንና ተጠያቂነትን በማጥራት በኩል ያላቸውን እምቅ አቅም ማስረዳት ይቻል ዘንድ ተዛማጅ የንድፈ-ሀሳብ እና የአካዳሚክ ጽሁፎች በትንታኔው ውስጥ ተካተዋል። የሚከተሉት ንዑስ ክፍሎችም ይህንን ምልከታ ለማጠናከር በመጀመሪያ የከንባታ ማህበረሰብ ባህላዊ ፍትህ ስርዓት ተሞክሮን በወፍ በረር ሲቃኙ፤ በመቀጠል ይህ ባህላዊ ስርዓት እውነትን እና ተጠያቂነትን ለማስፈን ያለውን አበርክቶ ፅንሰ-ሃሳባዊ እንድምታ ይፈትሻል። በመጨረሻም መሰል እሴቶች መደበኛውን የፍትህ ሥርዓት ለማጎልበት ስለሚኖራቸው ሚና በማጉላት ፅሁፉ ማጠቃለያ ይሰጣል።

## 2. የከንባታ ባህላዊ የፍትህ ስርዓት እና ትውፊት

የከምባታ ብሔረ-ሰብ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ውስጥ ባለው ከምባታ ዞን ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፤ ከምባቲሳ የሚባል ከኩሽቲክ ቋንቋ መደብ የሚመደብ ቋንቋ ይናገራሉ።[12] ግብርና የብሄረሰቡ ቀዳሚው የኑሮ መሰረት ሲሆን፤ በዋነኛነት የጥራጥሬ እህሎችን ጨምሮ እንሰት፣ ሙዝ፣ አቮካዶ፣ ድንች እና ዝንጅብል በማምረት ይታወቃል።[13] የከምባታ ሕዝብ ብዝሀነት ያለው የበርካታ ጎሳዎች ስብጥር ሲሆን፤ በዙሪያው ካሉት እንደ ሀዲያ፣ ጠምባሮ፣ ሲዳማ፣ ኦሮሞ፣ ሃላባ እና ወላይታ የመሳሰሉ ህዝቦች ጋር ጠንካራ የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ መስተጋብር አለው።[14]

ሙሁራን በተለይም ሲንገር (1975 እና 1980)፣ ሰይፉ (1970)፣ ያእቆብ (2002)፣ ኦንሳሞ እና ስሪላታ (2023) የከምባታን ባህላዊ ፍትህ ስርዓት በዝርዝር ጥናት አድርገዋል።[15] በጥናታቸውም፣ የከንባታ ሕዝብ ግጭቶችን ለመፍታት

---

[12] Hailu Tesfaye Habisso, *A Short History of the Kambata People of South-Western Ethiopia* https://citeseerx.ist.psu.edu/document?repid=rep1&type=pdf&doi=37fa64cb54ea6559945dad9b790b1cd291519e9c

[13] ከማህበረሰቡ አባላት ጋረ በተደረገ መደበኛ ያልሆነ ቃለ መጠይቅ እና ውይይት፤ ታህሳስ 22/2017 ዓም፣ ሐዋሳ።

[14] Ibid

[15] Daniel H. Onsamo and V. Srilatha, 'The Hadiya and Kambata Societies' Customary Dispute Resolution Mechanism in Ethiopia: A Systematic Review and Meta-Analysis' *Journal of Research in Humanities and Social Science*, Vol. 11, No. 4 (2023), pp. 275–280; Norman Singer, 'The Use of Courts as a Key to Legal Development: An Analysis of Legal Attitudes of the Cambata of Ethiopia' in Harold Marcus (ed.), *Proceedings of the First United States Conference of Ethiopian Studies, 1973* (Monograph No. 3, African Studies Center, Michigan State University, East Lansing, 1975), pp. 36–

የሚጠቀምበት በረጅም ዘመናት የዳበረ እና ከትውልድ ወደትውልድ በትውፊት ሲተላለፍ የቆየ ጠንካራ ሴራ (Seera) የሚባል ባህላዊ ፍትህ ስርዓት እንዳለው ያቀርባሉ::[16] ይህ ስርዓት "ማሬታ" (maretta) ወይም "ለእውነት መቆም" በሚል መርህ ላይ መሰረት ያደረገ ነው:: ይህ ባህላዊ የፍትህ ስርዓት አስተዳደራዊ ግዛት መሰረት ያደረጉ (administrative territory based) እና የጎሳ ሀረግ (kinship) ተከትለው ያሉ የባህላዊ አስተዳደር እና ፍትህ መዋቅሮችን አጣምሮ የያዘ ነው::[17] አስተዳደራዊ ግዛትን መሰረት አድርጎ ሄራ (*heera*)፣ ጎቲቾ (*goticho*) እና ኮኮታ (kokota) ወይም ጎጎታ (*gogota*) መዋቅሮች ሲገኙ፤ ሄራ (heera) በመንደር ደረጃ፣ ጎቲቾ (goticho) ብዙ ሄራዎችን በአንድነት በማካተት በአካባቢ ደረጃ፣ እንዲሁም ኮኮታ (kokota) ወይም ጎጎታ (*gogota*) ደግሞ ብዙ ጎቲቾዎች እና አካባቢዎችን አካቶ በከፍተኛ ደረጃ የተቋቋሙ ባህላዊ አስተዳደር እና የፍትህ መዋቅር እንደሆኑ ይነገራል::[18] ጎጎታ በከምባታ ማህበረሰብ ውስጥ ሰፊ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ፋይዳ ሲኖረው፤ ከሶስቱ ባህላዊ አስተዳደር እና ፍትህ ተቋሚት ውስጥ ከፍተኛ የስልጣን ደረጃ ያለው ነው:: በጎጎታ ተቋም የሚሰጡ ውሳኔዎች እንዲሁም ፍርዶች መጣስ እንደ ከባድ ጥፋት ሲቆጠር፤ ይህም እርግማን ይስባል ወይም ያስከትላል ተብሎ በማህበረሰቡ ዘንድ ይታመናል::[19]

---

83; Norman Singer, 'The Relevance of Traditional Legal Systems to Modernisation and Reform: A Consideration of Cambata Legal Structure' in Jean Tubiana (ed.), *Modern Ethiopia from the Rise of Menilek II up to the Present: Proceedings of the Fifth International Conference of Ethiopian Studies, Nice 1977* (A. A. Balkema, Rotterdam, 1980), pp. 537–556; Yacob Arsano, 'Seera: A Traditional Institution of Kambata' *The Challenge of Democracy from Below*, Vol. 45 (2002).

[16] Yacob Arsano, 'Seera: A Traditional Institution of Kambata' *The Challenge of Democracy from Below*, Vol. 45 (2002).

[17] Alula Pankhurst and Getachew Assefa, *Understanding Customary Dispute Resolution in Ethiopia* in Alula Pankhurst and Getachew Assefa (eds.), *Grassroots Justice in Ethiopia: The Contribution of Customary Dispute Resolution* (Centre Français d'Études Éthiopiennes, Addis Ababa, 2008), pp. 1–76.

[18] Daniel H. Onsamo and V. Srilatha, 'The Hadiya and Kambata Societies' Customary Dispute Resolution Mechanism in Ethiopia: A Systematic Review and Meta-Analysis' *Journal of Research in Humanities and Social Science*, Vol. 11, No. 4 (2023), pp. 275–280

[19] Abebe Demewoz Mengesha, Samson Seid Yesuf, and Tessema Gebre, "Indigenous Conflict Resolution Mechanisms among the Kembata Society." *American Journal of Educational Research*, vol. 3, no. 2 (2015): 225-242. doi: 10.12691/education-3-2-17.

ይህ ባህላዊ አስተዳደር እና የፍትህ መዋቅር ዝምድና ወይም የጎሳ ሀረግ (kinship) መሰረት አድርጎ ከተቋቋሙት የተለያየ የእርከን ደረጃ እና ሚና ካላቸው ሶስት የባህላዊ ፍትህ መዋቅሮች ማለትም ወሸቢ ዳና (woshebi dana)፣ ጋቾ ዳና (gacho dana) እና ዎማ (woma) ጋር የተሳሰረ ቁርኝት አለው። ወሸቢ ዳና (woshebi dana) በመንደር (village) ደረጃ እንዲሁም ጋቾ ዳና (Gacho dana) በወረዳ ደረጃ ለሚነሱ ግጭቶች ባህላዊ ዳኝነት እና ፍርድ የሚሰጡ ባህላዊ ዳኝነት መዋቅር ነዉ።[20] ዎማ (woma) በከምባታ ህዝብ እንደ ባህላዊ ንጉስ ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን፤ በዋናነት ከኦየታ ጎሳ የሚመረጥ እና ከፍተኛ ደረጃ ያሉ እና ከጋቾ ዳና (gacho dana)፣ ቦኮ (boko) እና ኢላሞ (ilamo) በየደረጃቸው በተሰጡ ፍርዶች ላይ ቅሬታ ያለው ወገን በሚያቀርባቸዉ ጉዳዮች ላይ ባህላዊ ዳኝነት የሚሰጥ ባህላዊ መዋቅር ነዉ።[21] ይህን የባህላዊ ፍትህ ስርዓትን ውስብስብ፣ ጠንካራ እና ተደራሽ የሚያደረገው፣ የባህላዊ ዳኝነት ስርዓቱን እሚያግዙ አልፎ አልፎ በተደራራቢነት የሚሰሩ ሚኔ (mine)፣ ቦኮ (boko) እና ኢላሞ (Ilamo) የሚባሉ የጎሳ ሀረግ (kinship) ስርዓት መሰረት ያደረጉ ተጨማሪ ተቋሚት መኖራቸው ነው። ሚኔ በቤተሰብ ደረጃ ያሉ ትናንሽ የግል ችግሮችን በቤተሰብ ደንቦች የሚፈታ አደረጃጀት ሲሆን፤ ቦኮ በጎሳ ደረጃ እንዲሁም ኢላሞ በብሄረ-ሰብ ደረጃ የሚነሱ ከፍ ያሉ ግጭቶችን በባህላዊ ሕግ እና በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፉ ደንቦች እና ልማዶች መሰረት ፍትህ የሚሰጡ ተቋሚት ናቸው።[22] ይህም የከምባታ ባህላዊ ፍትህ በክልላዊ አስተዳደር እና ጎሳ አመራር ውስጥ የተዋቀረ፣ በዘመናት ልምምድ ውስጥ የደረጀ እና በጥልቀት የተቀናጀ እንዲሁም በተዋረድ ተደራሽ የሆነ ባህላዊ የህግ እና የዳኝነት ማዕቀፍ እንደሆነ ያሳያል።

---

[20] Alula Pankhurst and Getachew Assefa, *Understanding Customary Dispute Resolution in Ethiopia* in Alula Pankhurst and Getachew Assefa (eds.), *Grassroots Justice in Ethiopia: The Contribution of Customary Dispute Resolution* (Centre Français d'Études Éthiopiennes, Addis Ababa, 2008), pp. 1–76.

[21] Daniel H. Onsamo and V. Srilatha, 'The Hadiya and Kambata Societies' Customary Dispute Resolution Mechanism in Ethiopia: A Systematic Review and Meta-Analysis' *Journal of Research in Humanities and Social Science*, Vol. 11, No. 4 (2023), pp. 275–280.

[22] Ibid

እነኚህ በየደረጃው የሚገኙ ባህላዊ ተቋማት፣ ባህላዊ መሪዎች እና ዳኞች ያላቸውን ባህላዊ ስልጣን፣ የሞራል ልዕልና እና ቅቡልነት በመጠቀም የባህላዊ ፍትህ ስርዓቱን እና ህጎቹን ለማህበራዊ ፍትህ እና ዘላቂ ሰላም እያዋሉት ይገኛሉ። በዚህም ሰፊ ልምድ እና ተሞክሮ ያደረጁ ሲሆን፤ እነኚህንም ባህላዊ ህጎች፣ ስርዓቶች እና ትውፊቶች ጠብቀው በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ እያስተላለፉ እዚህ ደርሰዋል። ይህም ቀልጣፍ የፍትህ ተደራሽነትን በማስፈን፣ የፍትህ ጥያቄ ያለው ግለሰብ ስርዓቱን ጠብቆ አቤቱታውን እንዲያሰማ ወይም ቅሬታ ካለው በየደረጃው ይግባኝ እንዲያቀርብ በማድረግ እንዲሁም ቅቡል እና ተገማች የማህበራዊ ፍትህ ስርዓት እንዲኖር አስቻይ አቅም አላቸዉ። ምንም እንኳን ይህ ባህላዊ ፍትህ ስርዓት ከመደበኛ ፍትህ ስርዓቱ ጋር ተጣምሮ እና ህጋዊ ስርዓት ተበጅቶለት በተጠናከረ መልኩ ግልጋሎት እንዲሰጥ ባይደረግም፤ በማህበረሰቡ ውስጥ ዛሬም ድረስ የጎላ ማህበራዊ ፋይዳ እና ፍትህ ጥያቄ ላይ ሰፊ ግልጋሎት እየሰጠ እንደሚገኝ ፅሁፎችም ሆኑ የማህበረሰቡ አባላት ይመሰክራሉ።[23]

ይህ የከምባታ ህዝብ ባህላዊ ፍትህ ስርዓት እውነትን ለማጥራት እና ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚያስችሉ በርካታ ህጎች፥ ትውፊቶች እና ስርዓቶች በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ ቆይተዋል። ከነዚህም መሃከል ለዚህ ጽሁፍ ግብዓትነት እና ምሳሌያዊ ማብራርያነት ያገለግል ዘንድ ከማህበረሰቡ አባላት ጋረ በተደረገ መደበኛ ያልሆነ ቃለ መጠይቅ እና ውይይት መሰረት የሚከተሉትን ሁለት ትውፊቶች አቀርባለሁ።[24]

---

[23] Daniel H. Onsamo and V. Srilatha, ‘The Hadiya and Kambata Societies’ Customary Dispute Resolution Mechanism in Ethiopia: A Systematic Review and Meta-Analysis’ *Journal of Research in Humanities and Social Science*, Vol. 11, No. 4 (2023), pp. 275–280; ከማህበረሰቡ አባላት ጋረ በተደረገ መደበኛ ያልሆነ ቃለ መጠይቅ እና ውይይት፤ ታህሳስ 22/2017 ዓም፣ ሐዋሳ።

[24] በዚህ ክፍል ውስጥ የቀረቡት ባህላዊ እና ትውፊታዊ ዝርዝሮች ከማህበረሰቡ አባላት ጋረ በተደረገ መደበኛ ያልሆነ ቃለ መጠይቅ እና ውይይት መሰረት በታህሳስ 2017 ዓም የተሰበሰቡ እና ለዚህ ፅሁፍ የዳበሩ እንደሆኑ ፀሃፊው ያስረዳል።

### 2.1. በባህላዊ ዳኝነት ላይ እውነትን ስለመፈልግ እና እውነትን መቀማት ያለው ተጠያቂነት

በባህላዊ ዳኝነት ስርዓቱ ተከራካሪዎች፥ የባህላዊ መሪዎች ወይም ዳኞች የሰጡት እዉነታን የማጠየቅ፤ ዳኝነትን በባህሉ መሰረት አመስግኖ የመቀበል ወይም በተቃራኒው እውነትን የተቀማው ውሳኔውን የመኮንን እና ባህላዊ እርግማን የማስተላለፍ መብት አላቸው፡፡ በመሆኑም በባህላዊ ዳኝነት ስርዓቱ እውነት እንዳልተፈረደለት ወይም እውነቱ እንደተቀማ ያመነ ተበዳይ "ቲ ገሪት ሚኒ'ኔ አጉ" ማለትም "ይሄ እውነት/ፍትህ እናንተ ቤት ይግባ" ብሎ ዳኝነቱ ላይ ያለውን ቅሬታ በእርግማን መልክ በመግለፅ ሐቁን አሳልፎ ይሰጣል፡፡ በዚህም ቅሬታ ያለው ግለሰብ ዳኝነት ሰጪ ለሆኑት ባህላዊ ዳኞች እውነት ወይም ፍትህ ስላልሰጣችሁ በቤታችሁ ወይም በራሳችሁ ኑሮ እውነት ወይም ፍትህ አታግኙ ብሎ ፍርዱን ለፈጣሪ የሚተውበት እና ለሰጡት ዳኝነት ከፈጣሪ ዘንድ ተጠያቂነት እንዳለባቸው የሚገልጹበት ስርዓት ነው፡፡ ይህንን ባህላዊ እርግማን ተከትሎ የባህላዊ ዳኛ/ዳኞች መኃከልም በእውነት ዳኝነት ላይ ቅሬታ ያለው/ያላቸው "እኔ የለሁበትም" በማለት ቅሬታውን ወይም የልዩነት ሃሳቡን (በዘመናዊው የፍትህ ስርዓት dissenting opinion የምንለው ዓይነት) በማቅረብ ከኢፍትሃዊና ፍርደ ገምድልነት ነው ብሎ ካመነበት ውሳኔ እራሱን ነፃ ያወጣል፡፡ በዚህም ለእውነት መቆም ስህተትን ያርማል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይህም በከንባታ ማህበረሰብ ውስጥ እውነትን ለማጥራት እና ማህበራዊ ፍትህ ለማስፈን መሠረት እንደሆነ በትውፊትነት ይነገራል፡፡

### 2.2. ከሰማይ ወርዶ እውነትን፣ ተጠያቂነትን እና ፍትህን ያሰፈነ መብረቅ ትውፊት (Myth)

የመብረቅ ፍትህ በከምባታ ህዝብ በሰፊው የሚታመን ትውፊት ሲሆን፤ በከምባታ ዞን በቃጫቢራ ወረዳ ወንድሬ ቀበሌ በአንድ ምስኪን ገበሬ እና ባለጠጋ መኃከል የተከሰተውን የድንበር ግጭትን በባህላዊ ዳኝነት ከመዳኘት ሂደት ጋር ተያይዞ በማህበረሰቡ በትውፊትነት የሚነገረውን ታሪክ ለዚህ ጽሁፍ እንደ ምሳሌ አቀርባለሁ፡፡ የግጭቱ መነሻ ባለጠጋው የእርሻ መሬት ድንበሩን ገፍቶ የደሀ ገበሬውን መሬት ወደራሱ አጠቃሎ “ድንበሬ እዚህ ድረስ ነው” ይላል፤ ይህንንም

 DOI: https://dx.doi.org/10.4314/hujl.v9i1.9

ደሀ ገበሬው ይቃወማል። ባለጠጋው እና ደሀው ገበሬ በባህላዊ ዳኝነት ስርዓት መሰረት ይህንን ግጭት እንዲዳኟቸው ጉዳያቸውን ለአካባቢው ባህላዊ ዳኞች ያቀርባሉ። በዚህም መሰረት የባህላዊ ዳኞች ጣልቃ ገብተው ሁለቱንም ወገን የሰሙ ሲሆን፤ በወቅቱ ፍሬ ነገሩን በቅጡ የማያውቅ መንገደኛ በጉዳዩ ጣልቃ ገብቶ ለባለፀጋዉ በመወገን እውነትን አጣሞ ምስክርነት ይሰጣል። ዳኞችም እውነቱን እያወቁ ለባለፀጋው አድልተው የገበሬውን ድንበር ቆርሰው ለባለፀጋው ፍርድ ሰጡ። እውነቱን የተቀማው ደሀው ገበሬ "ይሄ እውነት/ፍርድ እናንተ ቤት ይግባ" ብሎ ዳኝነቱን በመርገሙ መብረቅ ከሰማይ ወርዶ ድንበሩን እንዳሰመረ እና እውነትን እንደመሰከረ፣ ባህላዊ ዳኞችን እና የሀሰት መስካሪውን ፍትህ/እውነትን በማጣመማቸው ተጠያቂ እንዳደረገ እና ፍትህ እንዳሰፈነ ይታመናል። በዚህም ከሰማይ የወረደው መብረቅ ባህላዊ ዳኞች በቆሙበት እንደገደላቸው፣ ለእውነት መቆም እንዳለባቸው እና እውነትን አዛብተው በመወሰናቸው ተጠያቂነት እንዳለባቸው ሲያሰፍን፤ ባልተጠራበት ጣልቃ ገብቶ የውሸት ምስክርነት የሰጠውን መንገደኛ ጀርባውን ጠብሶ በሀሰተኛ ምስክርነቱ እንደቀጣው፤ መሬቱን መትቶ አከራካሪውን ድንበር እንዳሰመረው፤ የሀሰት ክስ ያቀረበውን ባለፀጋውን እዛው በቆመበት ንደገደለው፤ በተቃራኒው፣ ተበዳዩ ምስኪን ገበሬ ላይ አንዳች ጉዳት ሳያደርስ በሰላም እንደተወው ይነገራል። ይሄ የመብረቅ ፍትህ ትውፊት እንደ አፈ ታሪክ ሳይሆን መሬት ላይ እንደተፈጠረ እውነተኛ ታሪክ በማህበረሰቡ በሰፊው ይነገራል፤ እምነትም ይጣልበታል። ይህ አፈ ታሪክ በከምባታ ብሔሰብ የባህላዊ ፍትህ ሥርዓት ውስጥ ያለውን አበርክቶ በሚቀጥለው ክፍል ቀርቧል።

## 3. የከንባታ ህዝብ ባህላዊ ዳኝነት ስርዓት ለእውነት እና ተጠያቂነት ያለው ቦታ

### 3.1. የእውነት መሠረት እና እሴት

ከላይ የቀረበው ትውፊት እንደሚነግረን የከምባታ ብሔረ-ሰብ ባህላዊ ፍትህ ስርዓት መሰረቱ እውነት መሆኑ ነው (truth as justice)። በተመሳሳይ ሶቅራጦስ እውነት የፍትህ መሠረት እንደሆነ ሲከራከር፤ አርስቶትል በሐቅ ላይ የተመሠረተ "የእውነት ፍትህ" (truth as justice) የፍትሃዊ ስርዓት ፅንሰ-ሀሳብ መነሻው መሆኑን ያወሳል።

[25] በከንባታ ባህልም፣ አንድ ግጭት በሚዳኝበት ስርዓት ውስጥ የባህላዊ ዳኞች ዋና ተግባር እውነቱን ማግኘት እና ለእውነት መቆም መሰረታዊ እደሆነ ያስረዳል፡፡ ይህም ማለት ፍትህ ለማስፈን ዋነኛው ግብ "እውነትን ማግኘት" ሲሆን ይህም በባህላዊ የዳኝነት ሂደት ውስጥ በግልፅ ይታያል፡፡

በዚህ ባህላዊ ዳኝነት ስርዓት እና ሂደት ውስጥ፥ እውነትን ለማጥራት/ለመፈለግ በሚሳተፉት አካላት መካከል ያለው ግንኙነት ከየርገን ሀበርማስ ምክንያታዊ ግንኙነት (communicative rationality) ንድፈ ሃሳብ ጋር ሰፊ ቁርኝት አለው፡፡ ሀበርማስ እንደሚለው፥ በቅንነት እና እውነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ለግለሰብ አብርሆት (enlightenment) ብቻ ሳይሆን የህብረተሰብ ተስማሚነትን (societal harmony) ለማምጣት ከፍተኛ ሚና ሲኖረው፤ በህብረተሰብ ውስጥ ያሉ ውስብስብ ጉዳዮችን ለመፍታት አካታች (inclusive) እና ምክንያታዊነትን የተላበሰ ግንኙነት አስፈላጊነትም ያስረዳል፡፡[26] በከንባታ ባህላዊ የፍትህ ሂደት ውስጥ የማህበረሰብ እምነት እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ ይህ እሳቤም እውነትን በማግኘት ሂደት ውስጥ ተከራካሪዎች በእኩል የሚያሳተፉበት እንዲሆን፤ ባህላዊ ዳኝነት ሰጪዎችም እውነትን እና ምክንያታዊነት መሰረት ያደረገ ግንኙነት በመፍጠር እውነትን ማግኘት እንደሚችሉ ያመላክታል፡፡ በተመሳሳይ በከንባታ ባህላዊ ዳኝነት ትውፊታዊ ታሪክ መሰረት ባህላዊ ዳኞች ሁለቱንም ተከራካሪ ወገኖች እውነታ እና ሀቅ በጥልቀት እና እኩልነት እንዲሰሙ፣ እንዲመርምሩ እንዲሁም ተፈጥሯዊ እና ባህላዊ በሆኑ የጋራ እሳቤ/እምነት/እሴት ላይ የተመረኮዘ ምክንያታዊነት መሰረት ያደረገ እውነት ላይ እንዲደርሱ ሃላፊነት ይጥልባቸዋል፡፡ ይህም በባህላዊው የፍትህ ስርዓት ተከራካሪ አካሎችን በዳኝነት ሂደቱ በእኩልነት በማካተት/በማሳተፍ እና በማዳመጥ እውነትን ይፈልጋል፤ ህበረተሰቡ በረጅም ማህበራዊ መስተጋብር በጋራ ያደረጀውን ባህላዊ ህጎች እና ሞራል እሴቶች ላይ ተመርኩዞ ምክንያታዊነት ያደረጃል፤ ማህበራዊ ስምምነት ይገነባል፡፡ ዱርክሄም እንደሚለው ማህበራዊ አንድነት (social solidarity)

---

[25] Gregory Vlastos, 'The Paradox of Socrates' in Gail Fine (ed.), *The Oxford Handbook of Plato* (Oxford University Press, Oxford, 1991), pp. 127–148.

[26] Jurgen Habermas, *The Theory of Communicative Action: Volume 1: Reason and the Rationalization of Society* (Thomas McCarthy, trans., Beacon Press, Boston, 1984).

የሚገኘው በጋራ እሴቶች እና በማህበራዊ ስምምነቶች ላይ ተመስርቶ ሲሆን፤[27] ይህ ባህላዊ ዳኝነት ስርዓት እውነት የፍትህ መሰረት እንደሆነ ከማስረዳት ባለፈ እውነት አሳታፊ እና አካታች በሆነ ምክንያታዊ ግንኙነት ውስጥ እንደሚደረጅ ሲመሰክር፤ በረጅም ሂደት እውነትን መሰረት ያደረገ ማህበራዊ መግባባትን/ስምምነትን እና ዘላቂ ሰላምን ለማደርጀት ለማህበረሰቡ አጋዥ ይሆናል።

ይህ ባህላዊ ፍትህ ስርዓት ከተፈጥሮ ሕግ ንድፈ ሐሳብ (natural law theory) ጋርም ሰፊ ቁርኝት አለው። በ13ኛው ክፍለዘምን የነበረው ቶማስ አኪዩናስ እንደሚለው የተፈጥሮ ህግ ንድፈ ሐሳብ ሞራላዊ መርሆች ያሉት እና በተፈጥሮ ዓለም ውስጥ በፈጣሪ ወይም ልዕለ-ሰብ ኃይል (super natural power) የተጻፉ እና የሚተገበሩ መሆናቸውን ያስረዳል።[28] ከዚህ ጋር በተያያዘ በትውፊታዊ ታሪኩ ውስጥ የተካተተው የመብረቅ ጣልቃ ገብነት (intervention by lightning) የባህላዊ ፍትህ ስርዓቱ የተመረኮዘበትን የተፈጥሮ ኃይል ውስጥ እውነት ሊደበቅ እንደማይችል የሚነገረን እምነታዊ ትውፊት ነው። በመሆኑም ባህላዊ ዳኞች እውነትን ወደጎን አድርገው ለፈለጉት አድልተው ቢወስኑ ይህ በደል በራሳቸው ህይወት እና ኑሮ እንደሚከተላቸው ሲታመን፤ ይህም እውነቱ በተፈጥሮ ኃይል (መብረቅ) ተገልጿል። ይህ ክስተት በባህላዊ ፍትህ ስርዓት ውስጥ እውነት የማይቀበር እና የማይደበቅ መሆኑን አመላካች ነው። በተጨማሪም፣ ተበዳዩ ገበሬ "ቲ ገሪት ሚኒ'ኔ አጉ" ወይም "ይሄ እውነት/ፍርድ እናንተ ቤት ይግባ" በማለት ፍርዱን ለፈጣሪ አሳልፎ ሲሰጥ፤ እውነት ከሰው ልጅ ዳኝነት በላይ የሆነ ተፈጥሯዊ ወይም አምላካዊ ሃይል እንደሆነ የሚያስረዳ የጋራ የሆነ ማህበራዊ እሳቤ ነው። ጆን ፊኒስ እንደሚለው የፍትህ ስርዓቶች ካለንበት አለም ሞራላዊ እውነታዎች ጋር ሊታረቁ ይገባል።[29] እነዚህን እውነታዎች ከተፈጥሯዊ ህግ እና ሞራል ስርዓት

[27] Emile Durkheim, *The Division of Labor in Society*. In Social Theory Re-Wired (pp. 16-39), Routledge, 2016.
[28] Robert Pasnau, *Thomas Aquinas on Human Nature: A Philosophical Study of Summa Theologiae*, 1a 75–89 (Cambridge University Press, Cambridge, 2002).
[29] John Finnis, *Natural Law and Natural Rights* (Clarendon Press, Oxford, 1980).

ISSN (Print): 2664-3979 ISSN (Online): 2791-2752
https://journals.hu.edu.et/hu-journals/index.php/hujl
https://www.ajol.info/index.php/hujl

ጋር ለማስታረቅ በከንባታ ማህበረሰብ ባህላዊ ፍትህ ስርዓት ውስጥ ባህላዊ መሪዎች እና ዳኞች የጋራ ሞራላዊ እሳቤዎችን የሚጠብቁ እና አምላካዊ ፍትህ የማስፈን የሞራል ልዕልና እና ሃላፊነት እንዳለባቸው ያስገነዝበናል።

### 3.2. ተጠያቂነት

በሁለተኛ ደረጃ፣ ከላይ የቀረበው ትውፊት (Myth) የሚነገረን የከንባታ ባህላዊ ዳኝነት ተጠያቂነት ላይ የተመሰረተ የፍትህ ስርዓት መሆኑን ነው። ተጠያቂነት ከእውነት ጋር ተጣምሮ የማህበረሰቡ ባህላዊ ዳኝነት መሰረቱ፣ እሴቱ እንዲሁም በማህበረስብ ውስጥ ለዳኝነት ስርዓቱ ቅቡልነት ምንጭነት ይነግረናል። በመጀመሪያ ደረጃ በዚህ ትውፊታዊ ታሪክ ውስጥ፣ ባህላዊ ዳኝነት የሰጡት ሽማግሌዎቹ እና የሃሰት ምስክሩ ያለባቸው ተጠያቂነት በመብረቅ ተገልጿል። ይህ ተምሳሌት በከንባታ ባህል ውስጥ ፍትህን በሚያጓድሉ ባህላዊ ዳኝነት ሰጪዎች እና የሃሰት ምስክሮች ላይ የፈጣሪ ቅጣት እንደሚከተል የሚያሳይ ነው። ይህም የሚያስረዳን በባህላዊ የፍትህ ስርዓት ውስጥ ዳኞች ለሚሰጡት ዳኝነት በሰማያዊ ኃይል ተጠያቂ የሚሆኑ ሲሆን፤ ውሳኔያቸው በእውነትና ማህበረሰቡ ባደረጀው ህግ እና ስርዓት ላይ የተመሠረተ መሆን እንዳለበት ነው።

ይህ እሴት በዘመናዊ የህግ ስርዓት ውስጥ ከሚገኘው የዳኞች ግላዊ ተጠያቂነት በተቃራኒ፣ በከንባታ ማህበረሰብ ውስጥ ተጠያቂነት በማህበራዊ፣ አምላካዊ፣ እና ተፈጥሯዊ መንገድ እንደሚያረጋግጥ አስረጂ ነዉ። በዋናነት ባህላዊ ዳኞች ለውሳኔያቸው በሰማያዊ ኃይል የሚጠየቁ መሆናቸው ይነግረናል። ይህ ፅንሰ-ሀሳብ የኢማኑዌል ካንት የሞራል ተጠያቂነት (moral accountability) ንድፈ ሃሳብን ሲያትት፤ የሰው ልጅ ለሚያደርገው ማንኛውም ውሳኔ እና ተግባር በሞራላዊ ህግ (moral law) የሚጠየቅ ይሆናል።[30] ይህም በከንባታ ባህላዊ ዳኝነት ትውፊታዊ ታሪክ ውስጥ፣ የባለፀጋው እና የውሸት ምስክሩ በመብረቅ የተቀጡት አምላካዊ ፍትህ መገለጥ ማሳያ ትውፊት ነው። ይህ የሚያሳየው በዚህ ባህላዊ ፍትህ ስርዓት

[30] Immanuel Kant, *Groundwork of the Metaphysics of Morals* (HJ Paton, trans., Harper & Row, New York, 1964).

ውስጥ የሚሳተፉ ግለሰቦች ተጠያቂነት ከግላዊ እና ማህበራዊ ተጠያቂነት በላይ በሆነ በፈጣሪ ወይም በተፈጥሮ ሃይል የሚሰፍን እንደሆነ ነው:: በመሆኑም በከምባታ ማህበረሰብ ባህላዊ ዳኝነት ዉስጥ ፍትህ ሰጪዎች ለውሳኔያቸው በሰማይ እና በምድር (በማህበረሰብ ዘንድ) የሚጠየቁ ናቸው:: በመሆኑም በዚህ ባህላዊ ፍትህ ስርዓት ውስጥ ተጠያቂነት የማህበራዊ እና አምላካዊ ስምምነት መሰረት ያለው መሆኑን ነው:: ይህ የተጠያቂነት ስርዓት ፍትህን በማስቀደም፣ በቡድን ተጠያቂነት፣ በርኅራኄ ማሳመን እና በአምላካዊ እርግማኖች/በረከቶች ላይ በመተግበር ማህበራዊ ትዕዛዝን ያረጋግጣል::

## 4. መደምደሚያ

ጠንካራ ባህላዊ እና ማህበራዊ እሴት ያላቸው ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች በአብዛኛው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ውስጥ ሲገኙ፤ ከመደበኛው ወይም ዘመናዊው ፍትህ ስርዓት ጎን ለጎን የፍትህ ግልጋሎት በየአካባቢው እየሰጡ ይገኛሉ:: እነኚህ ባህላዊ የፍትህ ስርዓት በማስረጃ እና በተፃፈው ህግ አሰራር ብቻ ተመርኩዞ እውነትን ለማግኘት ከሚጥረው ከመደበኛው ወይም ከዘመናዊው የፍትህ ስርዓት በተቃራኒ በባህላዊ መግባባት፣ እምነት እና የሞራል ልዕልና ላይ ተመስሮት እውነትን የማውጫ እና ፍትህን የማስፈኛ መንገድ እንደሆነ የከምባታ ብሔረ-ሰብ ተሞኩሮ በምሳሌነት ያስረዳናል:: ከዚህ ጋር በተያያዘ መደበኛው ወይም ዘመናዊው የፍትህ ስርዓት በመርህ ደረጃ የግለሰብን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ መስተጋብር ለማስጠበቅ እና ለማስረፅ እንዲያመች ከተደራጁ የምዕራባውያን የፍትህ እሳቤዎች እና ስርዓቶች በስፋት የተወረሰ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ ባሳለፈችው ተሞኩሮ መሰረት መደበኛው የፍትህ ስርዓት በሚፈለገው ደረጃ አብዛኛውን የማህበረሰብ ክፍል ዘልቆ ሊገባ፣ የፍትህ ጥያቄ በተፈለገው ደረጃ ሊያሰፍን፣ አስቻይ የጋራ ማህበረሰባዊ እሴት ሊያዳብር፣ ቅቡልነት እንዲሁም ማህበራዊ ተስማሚነት ሊፈጥር እንዳልቻለ በሰፊው ይነገራል::[31]

[31] Alula Pankhurst and Getachew Assefa, Understanding Customary Dispute Resolution in Ethiopia in Alula Pankhurst and Getachew Assefa (eds.), Grassroots Justice in Ethiopia: The Contribution of

በሌላ መልኩ ባህላዊ የፍትህ ስርዓት ግለሰብን ዘርፈ ብዙ ከሆኑ የአንድ ማህበረሰብ የጋራ መስተጋብሮች ጋር በማጣጣም እና ከትውልድ ወደ ትውልድ በሚተላለፍ እና በረጅም ሂደት ውስጥ በሚደረጁ የጋራ እውነት፣ እሳቤ፣ እምነት፣ ትውፊት፣ ህግ እና ተሞኩሮ መሰረት የሚገነባ ነው፡፡ በተጨማሪም ከመደበኛው የፍትህ ስርዓት በተሻለ መልኩ ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች ማህበራዊ ቅቡልነት (legitimate) እና ተስማሚነት (compatability) ያለው እውነትን የማጥራት እና ተጠያቂነት የማስፈን አቅም አላቸው፡፡

በዚህ ጽሁፍ እንዳየነው የከምባታ ብሔረ-ሰብ ባህላዊ የፍትህ እና የዳኝነት ስርዓት ለእውነት መቆም አስፈላጊነት እና እውነትን መካድ የሚያስከትለውን ተጠያቂነት በሚመለከት ጠንካራ ባህላዊ እና ማህበራዊ እሴት እንዳለው ነው፡፡ በግለሰብ መብት እና በተፃፈ ህግ እና ስርዓት ላይ ብቻ መሰረት ካደረገው መድበኛው የፍትህ ስርዓት በተቃራኒ ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች እውነትን በባህላዊ መግባባት፣ እምነት እና የሞራል ልዕልና ላይ የተመሰረተ የጋራ ማህበረሰባዊ እሴት አድርጎ ይገልፃል፡፡ በባህላዊ ፍትህ እሳቤ ምንጩ የጋራ ማህበረሰባዊ እሴት፣ አስተሳሰብ፣ ባህል፣ እምነት እና የማንነት መገለጫ ትውፊት ሲሆን፤ ይህም በዘመናት ውስጥ በቃላት ልውውጥ እና የቀን ተቀን ተሞኩሮ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ነው፡፡ በመሆኑም ይህም ባህላዊ ህግ እና ስርዓት ጽንሰ-ሃሳባዊ ብቻ ሳይሆን ተፈጥሯዊ የሞራል ስርዓት እንደሆነ የከምባታ ብሔረ-ሰብ ትውፊታዊ ትርክቶች በምሳሌነት ያስረዳናል፡፡

ከህጋዊ ብዝሃነት እና ከተፈጥሮ ህግ ንድፈ ሃሳብ በመነሳት የህግ ህጋዊነት ወይም ገዢ እውነትነት ከረጅም ጊዜ የቆዩ የጋራ ማህበረሰባዊ ድርጊቶች፣ እውቀቶች ወይም ተሞክሮዎች እንደሚደረጅ ያስረዳል፡፡ ስለሆነም እውነት ሊረጋገጥ የሚችል

Customary Dispute Resolution (Centre Français d'Études Éthiopiennes, Addis Ababa, 2008), pp. 1–76; Getachew Assefa, 'Towards Widening the Constitutional Space for Customary Justice Systems in Ethiopia', *Culture and Social Practice,* No. 43 (2020); Asafa Jalata, 'Gadaa System and Oromo Resistance' *Journal of Oromo Studies*, Vol. 19, No. 1 (2012); Abera Jembere, Legal History of Ethiopia. Hamburg and London: Lit Verlag (2000).

(proven truth) ብቻ ሳይሆን ማህበራዊ ሰላምና ማንነትን ለማስጠበቅ እንዲቻል የጋራ እውቅና ሊሰጠው የሚገባ (collectively acknowledged) መሆኑን አስረጂ ነው፡፡ ይህም የሚያንፀባርቀው የባህላዊ ፍትህ ስርዓቶች እውነትን እና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን የፍትህ ማዕቀፍ እና ስርዓት ለመገንባት አስቻይ እሴቶቻችን እንዳላቸው እና የፍትህ እሳቤ ምንጮቻችን ሊሆኑ እንደሚገባ ነው፡፡

እንደ ከምባታ ብሔረ-ሰብ ያሉ ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች በፍልስፍና፣ በሕግ ሥርዓቶች በተለይም በብዙ ማህበረሰቦች ውስጥ ፍትህን እንዴት እንደሚያሳድጉ በጥልቀት ሊመረመሩ፣ ያሉባቸው ክፍተቶች ሊታረቁ እና በፍትህ ስርዓታችን እና ሀገረ መንግስት ግንባት ሂደት ውስጥ በሰፊው ሊካተቱ እንደሚገባ ይነግሩናል፡፡ በዋናነት መሰል ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶችን መርምረን መረዳት እና ማደርጀት፣ እውነት እና ተጠያቂነት ላይ ያለን እሳቤ እና የፍትህ ስርዓታችን ያለበትን ክፍተት ለመሙላት ማህበረሰቡ ከሚኖርበት እሴት እና እውቀት ጋር ማዋሃድ እና ማደርጀት ይገባናል፡፡

ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶቻችን ከማግለል ይልቅ ያላቸውን ፋይዳ ለይተን የፍትህ ስርዓቱን ለማጠናከር ከዘመናዊው ስርዓት ጋር በመቀላቀል ወይም ጎን ለጎን ለመጠቀም የሚያስችል ስርዓት እና አሰራር ብናበጅላቸው የፍትህ ስርዓቱን ለማጎልበት፣ ማህበራዊ ትስስር እና ሀገር በቀል ህግጋትን ለማጠናከር ያስችላሉ፡፡ ነገር ግን ይህ እንዲሳካ ስለ ሕግ ያለን ንቃተ ህሊና ለውጥ ይሻል፡፡ ይህም በዋናነት ባህላዊ ፍትህ ስርዓቶቻችን በጥልቀት በመረዳት እና በዘመናዊ ሕግ እውቅና ለተሰጣቸው መሰረታዊ የሰው ልጅ ሰብዓዊ መብቶች እንቅፋት ሳይሆኑ ካለን ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ነባራዊ ሁኔታ አንፃር የተሻለ እና ዘላቂ ፋይዳ እንዳላቸው የሚገነዘብ እና የህግ እና ፍትህ ማሻሻያ የሚያመነጭ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህ የከምባታ ብሔረ-ሰብ ልምድ የባህል ቅርስ ብቻ ሳይሆን እውነትን እንደ ማህበራዊ እርቅ እና ተጠያቂነትን እንደ ግንኙነት ፈውስ ያማከለ የህግ ማጎልበቻ ተሞኩሮ ነው፡፡

በመሆኑም መሰል ህይወት ያላቸውን ባህላዊ ፍትህ ስርዓቶቻችንን፣ ማህበራዊ ተሞኩሮዎቻችንን እና እውቀቶቻችንን በማደርጀት እውነትን እና ተጠያቂነትን ለማስፈን በፍትህ ስርዓታችን ውስጥ አገልግሎት ላይ ማዋል ይጠበቅብናል። እንዲህ ያሉ ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች የተለያዩ ማህበረሰቦች በረጅም ታሪካዊ ሂደት፣ ትስስር፣ እምነት እና የዳበረ ልምድ መሠረት የደረጁ እውቀቶች ሲሆኑ፤ ለዘመናዊ ህግ ስርአታችን መሠረት ካልሆነም ጎን ለጎን አጋዥ ሊሆኑ ይገባል። ፍትህን ከእውነት እና ተጠያቂነት ስርዓት ጋር አጣምረው የያዙ ሲሆን ሀቅ እና ተጠያቂነት እጦት እክል ውስጥ ለወደቀው ዘመናዊ ፍትህ ስርዓታችን ትልቅ ስንቅ ነው። በዋናነት የባህላዊ ዳኝነት ስርዓቱ ተቀባይነት ያለዉ፣ በፍቃደኝነት እና በእኩልነት ላይ የተመሰረት እዉነትን የሚመረምሩ እና ፍትህ የሚሰጡ የባህላዊ ዳኞችን ለተከሰቱ ጉዳዮች እንደየነባራዊ ሁኔታ እንዲቋቋሙ እድል ይሰጣል። ይህም ቀልጣፍ የፍትህ ተደራሽነትን በማስፈን፣ በተከራካሪዎች መኃል በእኩልነት ላይ የተመሰረተ በዳኝነት  ስርዓቱ ላይ ተሳትፎ እንዲኖራቸው በማድረግ እንዲሁም ቅቡል እና ተገማች የማህበራዊ ፍትህ ስርዓት እንዲኖር አስቻይ ስርዓት በመፍጠር ከግል ክርክሮች እና ውዝግቦች እስከ በቡድን መሃከል ለሚፈጠሩ የድንበር፣ የመሬት እና ተፈጥሮ ሃብት እና መሰል ግጭቶችን በቅጣታዊ እርምጃ (punitive) ሳይሆን ዘላቂ ማህበራዊ ሰላም እና ግንኙነት የሚመልስ ፍትህ ስርዓት (restorative justice) ለመገንባት ያግዛሉ።

## Conflict of Interest

The author, who is Editor-in-Chief of HUJL, declares that the peer-review process of this contribution followed a special procedure to prevent conflicts of interest, as per article 27 of HUJL's Editorial Policy, ensuring double-blind peer review under the control of the Managing Editor and Editorial Board members of the journal.